# የአዲሲቷ ኢትዮጵያ

# ልጅ

## ለአቶ ኦባንግ  ሜቶ የተበረከተ

*Dedicated to Ato Obang Metho*

**የአዲሲቷ ኢትዮጵያ ልጅ፣**
**የጋምቤላው ተወላጅ፣**

**አንተ ኦባንግ ኦ ሜቶ !**
**ምንድነው ከቶ**

**የህይወት ምስጢሩ**

**ኧረ እንቆቅልሹ? !**



Obang Metho speaking in Las Vegas

ገና ሳይህ ቁመና መልክህ
መሰለኝ ልጄን
ያሬድ ፑሽኪንን !

ደስ ብሎኛል እኔ
ያለወትሮዬ ዛሬ !

ፍልስፍናህ ከፍልስፍናዬ
ህልምህ ከህልሜ

በጣም ተስማማ
ንግግርህን ስሰማ !

ጨዋታና ቀልድህም
አለው ለዛ ጣእም !

ቅላፄ ባለው —አማርኛህ
ድንቅ በሆነው እንግሊዝኛህ !
ንገርልኝ አዎን
እቅጬ እቅጩን፣
Birth is a Biological
Accident መባሉን!
አበውም መወለድ
ቋንቋ ነው ያሉትን !
አዎን እንዲህ ንገርልኝ
ሃቁን አፍርጥልኝ !
ቋንቋና ሃይማኖትም
ዘርና ጎሳም፣
ያካባቢ ግኝት
ያጋጣሚ ውጤት
ሰው ሰራሽ መሆኑን !
አይደለም የተፈጥሮ
የሚወለድ አብሮ !
አዎ ! - ዋናው ቁም ነገር
ሰው ሆኖ መፈጠር !
ሰው ለሰው መኖር !
ሰውን በሰውነቱ ማክበር !

እሰይ አስተምረው ወጣቱን ትውልድ !
«አንድለሁሉም ሁሉም ላንድ፣One for all, all for one»
ዘብ  ይቁም በለው - ለህግ የበላይነት፣
ለሰላም ለፍቅር ለሰብኣዊ መብት፣
ለኢትዮጵያ አንድነት ለሃገር እድገት !

ረሃብ ችጋር ቸነፈር፣
ጦም ውሎ ማደር፣
ቀን አይሰጤ ነው በልልኝ !
አባይ ይቆይ ይደርልኝ !

ለታሪክ እስረኞቹ !
ለትምክተኞቹ ! ለጠባቦቹ !
እሰይ ! እንዲህ ንገርልኝ ! አንጀቴን አርስልኝ !
ያለፈውን ትተው
ተባብረው ጋግረው፣
ድፎ ዳቦ ይብሉ !
በሙልሙል አይጣሉ !

ንገርልኝ በሞቴ !
ቅቤ ይጠጣ አንጀቴ !
አዎ ! - አገር ጫት አይደለም !
አይቀነጠስም ! - አይቀነጠብም !
መሬት ጫት አይደለም ! ለጠላት ለባዳ አይቸበቸብም !

ጎሽ የኔ አንበሳ
የኢትዮጵያ እምቦሳ !
አዎ ንገራቸው
እስቲ ምከራቸው
ለነ ሰው ጤፉ
ለነ አፄ በጉልበቱ !
አንተን ጭቁኑን

«ነፍጠኛ»ያልሆንከውን
ምናልባት ቢሰሙ - ቢማሩ!
እንደበት - ልቦና ቢገዙ!
የቂም በቀል ጦሱ
የጥላቻ መዘዙ
ውሎ አድሮ እንዳይተርፋቸው
ለልጅ ልጆቻቸው!!!

በል ውድ ወዳጄ አባንግ፣
በቸር ይግጠመን በደግ፣
«ሰላም ለከ»ልበልህ፣የህይወት ጉዞ ይቅናህ!!!

***




አሰፋ ገብረ ማርያም ተሰማ
የቀድሞውየኢትዮጵያ ህዝብ መዝሙር «ኢትዮጵያ ቅደሚ» ደራሲ.

<u>ማሳሰቢያ</u>

ግጥሙ አቶ ኦባንግ ኦ ሜቶ በላስ ቬጋስ «የኢትዮጵያ ራእይ ማህበር»እንግዳ ሆኖ ንግግር ባደረገበት በኦገስት 16 ቀን፣ከስብሰባና ከእራት ግብዣ መልስ ሌሊት በትኩስ ስሜት እንደወረደ የተፃፈ ነው።አንባብያን ግጥሙን ስታገኙ እባካችሁ ለሌሎች አንባቢዎችም በተመቻችሁመንገድ አዳርሱት በኦባንግ ኦ ሜቶ ሞት! - Do smile please ገጣሚው።